# መቅድም

አባይ አጋፋሪ

የዉሃዎች ጋሰሪ ቢሻን ጋሪ

የትየለሌ ኩሬዎች፣ መስኖዎች ስብጥርጣሪ

አባይ ካርቱም ተፈጣጥሞ

ካይሮ የሚፋታ

ሮዜታ ዳሜታ

የሃበሻዉ ምድር የሰከላ ፈለቅ

የሰም አፈርዋ መረቅ

የእልፍ ጅረቶች ዝንቅ

የሱዳን የግብጥን በረሃ ሲያገንት

እንደምን እምዬ ደርቃ ገጥጣ ትሙት?

አባይ

ተፈጥሮ፣ ብርሀን ፣ ምግብ፣ህይወት

የሰዉ የእንስሳ፣የአራዊት

የሀገራት መቅረዝ

እንደምን ብርሀኑ ይክዳት?

**************

በአባይ ጉዳይ

ከማን ይኳረፉ? ከማን ይገለሉ?

ምንድንስ ፉከራ?

ቀረርቶ ጌረራ?

በአባይ ዕንሱ፣ ዉልደቱ፣ዕድገቱ

ቢኖሩ እኮ ነዉ....ጭልፊትና አሞራ

ታድያንን የሁላችን እንጅ የማነዉ አንጡራ?

************

የአምባ ጌጥ ኩራት ትምክህት

የዉልድ ዕድገት ምድርህን ሳታስደስት

ቤተሰቡን ሳይመግብ

ለባዕድ እንደሚንገበገብ

ተገብዘህ ኖረህ ኖረህ

ዛሬ ፊትህን ስታዞር ወደ ምድርህ

የህዝብህ ቁጭት ቁርጠኝነት ማርከህ

ከቶ እንደምን ልትሆን ጦር መሳበቂያ

ላንቃ ማላቀቂያ?

መቼ ከወንዙ አምላክ 'ሀፒይ'

ወይ ከጦር ሰበቃ

ከትብብር መንፈስ ነዉይ ፋይዳ!

እንጂማ፥ ጅል ነዉ ምጽደቃ!

እነሆ ግብጦች

እንደ ሀቅ በሦስት ቋንቋ

የሚጮህ ዉሻ አይናከስም

ሳሬን ዱቱ ናማኛቱ፡

፤ ዶግ ዛት ባርክ ነቨር ባይት

እንደ ታሪክ ሀቅማ

አይታበል አይታማ

ግብጥን ያረሰረሰ አባይ

ያኔ ያኔ ዱሮ ደም በደም የሆነ

መች በአቢሲንያ ምድር

መች በደርቡሽ ሀገር እንጂማ በምስር

በፈጣሪ ትዕዛዝ በሙሴ አሮን በትር!

*************

ምነዉ ግብጦች ከአንተ ቢማሩ አባይ!

ጣና አባይን ሰላ ብሎ ተቀብሎ

አክብሮ ሲሸኘዉ ሰላ በል ብሎ

ደሞ ደሞስ

ጎረቤት ወዳዱ ካርቱም ላይ ሲገናኝ

ቀለም፣ ህብር፣ ስንቅ ከለሴዉ ጎረቤቱ

ምንም ባይመጥነዉ ዕንቁ ባይኖረዉ በቋቱ

በፍቅር አቅፎ በአንድ ስም መጠራቱ

በሳል እንጂ አባይ 'ዲፕሎማቱ'

**********

አባይ የህዝቦች ተዋፅኦ አርማ

በመዋጮ ከብረህ ጎልብተህ ፈርጥመህ

ነጩን፣ቀዩን ፣ጥቁሩን በአንድ የምታስማማ

ቅኔህ ቢሰወርባቸዉ

የግብጥ ምሁር ሁላ ታማ!

**********

መቼም የአቤ...ምናብ ዕንስ አይደል ህዳሴዉ

መወለድ እንጂ የናፈቀዉ

ምዉት ያሉት ህዝብ ሁኖ ቅሪት

ምጡን ሲረሳ ጭንቁን አልፎ

ዉብ አዲስ እንቦቀቅላዉን ታቅፎ

ህዳሴ... እሹሩሩ

በሀሴት ሲያፍለቀልቅ የደስታዉ ሲቃ ሲያንፈቀፍቅ

እልልታዉ ሉሊቱን ሲያነቃንቅ

ሁኖ መገኘት የታሪክ ምርቅ እነደምን ያስቅቅ

እነሆ ግብዣ ለምስሮች

ሲንገማሸል የኖረዉ አባይ

በተንጣለለዉ እልፍኙ በግርማዉ ሲቃኝ

በብርሀኑ ጨለማን ሲዳኝ

በጉያዉ በረከት በዓሳ ምርቱ ሲናኝ

ቱሪስት ሆነዉ መጥተዉ በጀልባ ተንሸራሸረዉ

ናይል ፐርች አጣጥመዉ

በጢስ አባይ ነፍሳቸዉን አረስርሰዉ

የአባይ ጣና ቀኔን ፈትተዉ

ወንድም ይወለድለት መርቀዉ

ዘና እንዲሉ ምኞቴ ነዉ

አባይ አባይ የደርቡሽ የምስር ሲሳይ

ተብሎ በልጆቹ እንዳልታማ

ዛሬ፣ ነገ፣ ከዚያ በስትያም ልጆቹን እነዳያማ

በአባይ አድባሩ ጃርሳ ቢያ ጎበዝ እንስማማ!

ይሁን ይሁን ኬ ኤ ኤ ኤ ኤ ኤ ኤ ር!

ኬር በሉ! ኬ ኤ ኤ ኤ ኤ ኤ ኤ ር!

***********

ተፈሪ ተረፈ

16/01/2007 ዓ.ም

ለ ገ.ኢ/ጎርፉ